የሰ/መ/ቁ. 51790

ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- 1. እነ ወልዳይ ዘሩ (61 ሰዎች) - ጠበቃ ዳንኤል ብርዬ ቀረቡ

2. አቶ ቴዎድሮስ ይልማ - የቀረበ የለም

3. አቶ አማረ ተረፈ - " "

4. እነ አቶ ጀማል አህመድ (ሶስት ሰዎች) - የቀረበ የለም

5. አቶ ትግስቱ ጥላሁን - የቀረበ የለም

6. አቶ ቀዳማዊ ረታ - የቀረበ የለም

7. እነ አቶ አሰለፈው ገድፍ (ሁለት ሰዎች) የቀረበ የለም

8. እነ አሸናፊ አማረ (ሁለት ሰዎች) - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ እስከዳር አዘዘው ቀረቡ፡፡

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ በመ/ቁጥር 51789፣ 51792፣ 51794፣ 51798፣ 53301፣ 53460 እና 57247 ከቀረቡት ጉዳዮች ጋር ተመሳሳይ የሕግ ጥያቄ ያለበት በመሆኑ መዝገቦችን አንድ ላይ አጣምረን በመመርመር ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37/1/ መሠረት ሠራተኛን በልዩ ሁኔታ ከሥራ ስለማስናበት የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀረቡት የአሁኑ አመልካቾች ናቸው፡፡ የአመልካቾች አቤቱታ ይዘት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እየተገበረ ባለው የመሠረታዊ አሰራር ሂደት ለውጥ ምክንያት ምደባ ሳያገኙ የቀሩ በመሆኑ እረፍት እንዲወስዱ መደረጉንና ለአስራ አንድ ወራት ደመወዝ ሲከፍላቸው ቆይቶ ሐምሌ 01 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውላቸው ተቋርጦ ከስራ መሰናበታቸው ከሕግ ውጪ መሆኑን ገልፀው ወደ ስራ እንዲመለሱ፣ ይህ የማይሆን ከሆነ

ከስራቸው የተሰናበቱበትን ምክንያት በአግባቡ በመግለፅ የአመልካችን የመሰማት መብት ተግባራዊ በማድረግ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጣቸው ይወሰንላቸው ዘንድ የይግባኝ አቤቱታውን ማቅረባቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በተደረገለት ጥሪ መሠረት የአሁኑ ተጠሪ ቀርቦም እርምጃው በአዋጅ ቁጥር 578/2000 አንቀፅ 19/1/ለ/ እና በደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37/1/ መሠረት የተከናወነ በመሆኑ ተገቢ ነው በማለት የአመልካች ይግባኝ ውድቅ እንዲሆን ገልፆ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የአስተዳደር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የአመልካቾችን ይግባኝ በድምጽ ብልጫ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኛቸውን በተለያዩ መዛግብት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/337 መሠረት ይግባኛቸው ተሰርዞባቸዋል የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ከላይ በተጠቀሱት መዛግብት አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡ ሲሆን የአቤቱታቸው መሠረታዊ ይዘትም አመልካቾች የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ያረጋገጠልን የመደመጥ መብት ሳይከበር የተሰጠ የባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ጉዳያቸው ባግባቡ እንዲጣራ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት አመልካቾች የተሰናበቱት በሕጉ አግባብ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37/1/ እና /2/ አንጻር ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን የግራ ቀኙ የቃል ክርክር መጋቢት 10 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት በተወሰኑ መዛግብት ሲያሰሙ በተወሰኑ መዛግብት ደግሞ የጽሑፍ ክርክር ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢና ጉምሩክ ባለስልጣን ሠራተኞች መስሪያ ቤቱ በአዲስ መልክ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተብሎ ሲዋቀር የባለስልጣኑ መስሪያ ቤት የሰራተኞችን መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37/1/"ን" በመጥቀስ አመልካቾችን ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን ሲሆን አመልካቾች ይህ የተጠሪ እርምጃ ሕጋዊ አይደለም፣ በሕገ መንግስቱ የተከበረውን የመሰማት መብት የሚጥስ ነው በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሠረቱ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37/1/ ድንጋጌ በግልፅ የሚያሳየው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚሁ የሕገ መንግስት ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ፍርድ ቤቶች አንድን ጉዳይ (አቤቱታ) ተቀብለው ውሳኔ መስጠት የሚችሉት ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በሕግ ለሌላ አካል ያልተሰጠ ጉዳይ በሚሆንበት ጊዜ እንደሆነ መሆኑን ነው፡፡ በህግ ተለይተው በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲቋጩ በተባሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍርድ ቤት የመዳኘት የስረ ነገር ስልጣን ስለሌለው በሕጉ መሠረት ለአንድ አስተዳደር አካል ቀርቦ አስተዳደራዊ ውሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ ወይም ለአስተዳደር መቅረብ የሚገባውን ጉዳይ ፍርድ ቤት ሊያሰተናግደውም ሆነ አከራክሮ ውሳኔ ሊሰጥበት አይችልም፡፡ ለአንዳንድ የመንግስት አካላት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን የሚሠጡት

ሕጎች መጠበቅና መከበር ያለባቸው ሲሆን የዳኝነት አካል ስልጣንም በሕግ የተወሰነ ስለሆነ ሕግ የመተርጎም ስራው በሕጉ በተመለከተው አድማስ የሚመራ ይሆናል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 4 ድንጋጌ የሚያሳየውም ፍርድ ቤቶች በሌላ ህግ በግልጽ በታገዱ ጉዳዮች ላይ አከራክሮ የመወሰን ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በአስተዳደራዊ ውሳኔ የመጨረሻ እልባት እንዲያገኙ በህግ ተለይተው የተቀመጡት ጉዳዮችን ፍ/ቤቶች የመዳኘት ስልጣን የሌላቸው መሆኑ ሊስተዋል የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 79/1/ እና 37 ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲታዩ ፍ/ቤቶች አንድን ጉዳይ ተቀብለው ለማየትና ለመወሰን ሥልጣን የሚኖራቸው ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው (Justiciable matter) ሆኖ ከተገኘ ብቻ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አዋጅ ቁጥር 578/2000 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንን ያቋቋመ ሕግ ሲሆን በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 19/1/ለ/ ድንጋጌ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ቢኖርም የባለስልጣኑ ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይመራል በሚል በኃይለ ቃል ተደንግጎ ይገኛል ፡፡ በዚሁ ሥርዓት መሠረትም የሚኒስሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 ያወጣ ሲሆን በዚህ ደንብ አንቀጽ 37/1/ ስር በደንቡ በሌላ ሁኔታ የተደነገገ ቢሆንም ዋና ዳይሬክተሩ በሙስና የተጠረጠረውንና እምነት ያጣበትን ማንኛውንም ሠራተኛ መደበኛውን የዲስፕሊን እርምጃ አፈጻጸም ሥርዓት ሳይከተል ከሥራ ማሰናበት እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ከላይ በተመለከተው ስርዓት መሠረት ከስራ የተሰናበተ ሰራተኛ በየትኛውም የፍርድ አካል ውሳኔ ወደ ስራ የመመለስ መብት እንደማይኖረው አስገዳጅነት ባለው መልኩ አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሰራተኞች የሚተዳደሩት አዋጅ ቁጥር 578/2000 "ን" ተከትሎ በወጣው ደንብ ቁጥር 155/2000 መሠረት እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በደንቡ አንቀፅ 37/1/ መሠረት የሥራ ስንብት ቢፈፀም በዳኝነት በፍ/ቤት እንደማይታይ በተጠቀሰው ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በመርህ ደረጃ ሕግ የማውጣት ሥልጣን በሥልጣን ክፍፍል መርህ መሠረት የሕግ አውጪው አካል ስለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በሕግ አውጪው የመንግስት አካል የሚወጡ ሕጎች ቀዳሚዊ (primary legislations) ተብለው የሚታወቁ ሲሆን ሌሎቹ እንደአስፈላጊነታቸው አግባብ ባለው አካል የሚወጡ ሕጎች የበታች ህጎች (subsidiary legislations) ተብለው የሚታወቁ ናቸው፡፡ ሕግ አውጪው የመንግሥት አካል በተለያዩ ቴክኒካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ምክንያቶች ቀዳሚውን ሕግ ለማስፈጸም የሚያስችሉ ዝርዝር ሕጎች ያስፈልጋሉ ብሎ ባመነ ጊዜ ተገቢ ነው ላለው አካል የበታች ሕጎችን እንዲያወጣ ሥልጣን ሲሰጥ ይስተዋላል፡፡ ይህ አሰራር በሕግም በምክንያትም የተደገፈ እና የዳበረ ልምድ ስለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣው ደንብ ቁጥር 155/2000 ሕግ አውጪው በሰጠው ስልጣን መሠረት የወጣ ሲሆን በደንቡ አንቀጽ 37 መሠረት ደግሞ ሰራተኛው ከስራ የሚሰናበትበትን አግባብ ደንግጓል፡፡ በመሆኑም ወደ ስራ የመመለስ ወይም የመደመጥ መብት በፍርድ የሚያልቅ ጉዳይ አለመሆኑን የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ ከላይ እንደተገለጸው አንድ ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚችለው ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በሕግ ለሌላ አካል ያልተሰጠ ጉዳይ በሚሆንበት ጊዜ እንደሆነ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካቾች የተሰናበቱት ሕግ አውጪው በዘረጋው ሥርዓት መሰረት ሲሆን አመልካቾች ከጠየቁት ዳኝነት አንጻር (ወደ ስራ መመለስ ወይም የመደመጥ መብት መከበር) ሲታይ ጥያቄው በፍርድ ሊያልቅ የሚችል (justiciable matter) አይደለም፡፡

በመሆኑም የአስተዳደር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት የአመልካቾችን የይግባኝ ቅሬታ በአብላጫ ድምፅ ውድቅ ማድረጉ በአመልካቾች ከተጠየቀው ዳኝነት (ወደ ስራ እንድንመለስ ወይም የመደመጥ መብታችን ይጠበቅልን ከሚለው) አንፃር ሲታይ በአዋጅ ቁጥር 578/2000 አንቀጽ 19/1/ለ/ እና ከሚኒስተሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37(1 እና 2) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም አላማን የተከተለና ለአስተዳደር አካሉ በሕጉ አግባብ የተሰጠውን ስልጣን (executive prerogative) ያከበረ ነው ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ያለ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁጥር 00827/2001 ነሐሴ 18 ቀን 2001 ዓ/ም ጳጉሜ 02 ቀን 2001፣ በይ/መ/ቁጥር 00831/2001 ነሐሴ 18 ቀን 2001 ዓ/ም በይ/መ/ቁጥር 00839/2001 ነሐሴ 26 ቀን 2001 ዓ.ም፣ 00833/2001 ነሐሴ 26 ቀን 2001 ዓ.ም፣ በይ/መ/ቁ 00826/2001 ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም እና በይ/መ/ቁጥር 00828/2001 ነሐሴ 13 ቀን 2001 ዓ/ም እና በይ/መ/ቁጥር 00830/2001 መጋቢት 08 ቀን 2002 በአቶ አሸናፊ አማረና በአቶ አወቀ ተሻለ ጉዳይ ተሰጥተው በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀኑት ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 348(1) መሠረት ጸንተዋል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ተጣምረው እንዲታዩ ከተባሉት መዛግብት ጋርም ይያያዝ ብለናል፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

እ/ብ